ሶባሐል ኸይር!

4ኛ ዕትም



በሙሐመድ ሰዒድ (ABX)



ሶባሐል ኸይር!

በሙሐመድ ሰዒድ

መግቢያ

የዚህ መጽሐፍ መግቢያ እንዲህ የሚል ሊሆን ቻለ ...

“የምትናገሩትም ሆነ የምትጽፉት ነገር ታሪካችሁ ነው፤ ከዕድሜያችሁ በላይ ምድር ላይ ሊቆይ ይችላልና በጥንቃቄ ፃፉ፣ ተናገሩም::” ተብሏል::

ወዳጆቼ! እኔ ምናልባት በምድር ላይ የስልሳ እና ሰባ ዓመት ዕድሜ ሊኖረኝ ይችላል:: ይህ መጽሐፍ ደግሞ ከዚያ በላይ ይቆይ ይሆናል ማን ያውቃል:: ስለሆነም በርሱ አበርክቶ ትንሽ ዕድሜዬ ቢረዝም ብዬ ይህንንም መጽሐፍ በተቀሩት ሌሎች መጽሐፎቼ ላይ ጨመርኩ:: የሚዘልቅ መልካም ሥራ ሟችን የሚጠቅም ሁለተኛ ዕድሜ ነዉና:: አላህ ያዝልቀው::

መጽሐፉ በዋናነት ሰዎች ከፈጣሪያቸው አላህ ሱ.ወ. አንፃር መልካም ጥርጣሬ እንዲያሳድሩ (ተፋኡል እንዲኖራቸው)፣ በዱንያ ሕይወታቸው እንዲበረቱና ተስፋ እንዳይቆርጡ፣ ዱንያንም በብልሃትና በጥንካሬ እንዲሻገሩ ሀሳብ ይሠጣል፣ መንገድ ይጠቁማል:: በየትኛዉም ከባድ የዱንያ ማዕበል ዉስጥ ብትሆኑ ፊትለፊታችሁ ብሩህ ነው አብሽሩ አትፍሩ ይላል:: ወዳጆቼ ... ምክሩና ምልከታው ከናንተም በላይ ለኔ ያስልጋል:: እኔን ፀሐፊዉን፤ እናንተን አንባቢዎችንም ተጠቃሚዎች ያድርገን::

ከዚህ መጽሐፍ ዝግጅትና ሕትመት ጋር ተያይዞ የወንድም ጋዜጠኛ ዐብዱረሒም ኢሕመድ ያላሰለሰ ድጋፍ አለበት:: አመሰግኑልኝ ፤ ዱዓም አድርጉለት::

ወዳጆቼ ሁሌም በዱዓችሁ አስቡኝ::

የናንተው ሙሐመድ ሰዒድ ነኝ -

(የመጽሐፍ አዘጋጅ እና ተርጓሚ እንዲሁም በሳንደር ዩኒቨርሲቲ መምህር::

ታህሳስ 2016

ማውጫ

ለዎችን በምንችለው ሁሉ ማገዝ 10

አቀራረብን ማሳመር 12

ሰባሐል ኸይር..... 14

ለምን ሰባሐል ኸይር !! 16

ኢማም አሕመድን መሆን ባትችል እንኳ አበልሀይሠምን ሁን! 19

ተመልሰናል ጌታዬ (ነ) 20

ባይወድህማ ኖሮ 22

ፈማ ዘኑኩም ቢረቢል ዓለሚን..... 23

እያረፍን እንቀጥላለን 24

አላህን የመታዘዝ ትሩፋቶች..... 25

ባየሁት ወይስ በሰማሁት ነገር ልምከርህ 26

የማይሞሉ ክፍተቶች 27

ለኸይር ነው ወዳጄ..... 29

ጀነትን አስቡ..... 30

አላህ ያለ ቀን 33

ከትላልቅ ጂሃዶች መካከል..... 34

ምርጡን ምርጫህን ልንገርህ..... 36

ለአላህ የሆነው ይዘልቃል!..... 37

የሲትር ፀጋ..... 39

ራሱን የማይጥለው ጉቁው መአሚን ... 40
ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር ... 41
ተረጋጉ እንጂ ... 42
የአለመቻል ህመም ... 43
ሕይወት እንደዚሁ እኮ ናት ወዳጄ 45
በጭፍን የመከተል ጥፋት 46
ወንድም እህትን ማንበብ ... 47
በምን ዳንክ 49
እንደትላልቅ ሕፃናት ... 50
የመዘግየት ቅጣት ... 51
ዉለታን አለመርሳት 53
ነሕኑ ቀሰምና በይነሁም መሚሸተሁም 54
ለቀልብዎ ርጥበት ... 55
አደገኛው ገዳይ ... 57
ሕልምህን ለሚወድህ ሰው ብቻ 58
አይረሴው የመከራ ቀን 59
ብንሄድ ይሻላል ... 62
ደወል (1) ... 63
እኔ ያንተው ድሃ 64
መጀመርያኑ አለመጀመር 66

ለብሸር ወንድሜ 67
ወደ አላህ መሄድ 69
አንዳንዴ መጨከን ግድ ይላል 70
ስለየትኛው አምላክ ነው የምታወሩት? 72
የተፃፈ ቀደር ይቀየራል እንዴ 73
እኛንም ዱንያ ትዞረናለች እኮ 75
መለያየት ክፉ 76
ሰዎችን ከኃጢአት እንዳይወጡ ማገት... 77
እስቲ ተመኙ 80
ዲን የማይመስል ነገር 81
የፅናት ተምሳሌቷ እመት ዓኢሻ 82
ባሮቹን አታሳዝኑ 83
ለምን እኔን ብቻ 84
አዉታ ላንተም አለ በታ 87
የማይቀሩ ጎብኚዎቻችን 89
ሰው በኒያው ብቻ ካለመው ምኞት ይደርሳል 91
አላህ ሲጠላህ 93
እንቁልልጭ 96
ከአላህ አንፃር 97
የሰው ዉስጡና ዉጪው 98

የልቦና ንፅሕና 100
ለነቢዩ ኢብራሂም ዐሰ. ንግሥናን የሠጠው አላህ ነው!! 101
ዱንያ ዘዋሪ 103
ተመልሰናል ጌታዬ (2) 104
ዘምዘም አኬ... 106
ቂምና ኩርፊያ 108
ለካ ዝምብዬ ነው 109
አሪጅናል አይከዳም 110
ቁጣዉን የቀደመችው ረሕመቱ 111
ወንድ ልጃችሁን ስጡን 113
መይሙና ቢንት አል-ሓሪሣ 115
ድንገቴ ሪዝቅ 116
እርምት ስድብ አይደለም 118
በሰው እጅ መለካት 121
ኩሩ ሙስሊም ሁኑ 122
ሞትን ትፈራላችሁ እንዴ! 123
በአገላለጽ ማማር 126
በሁለት ጀናዛዎች መካከል 127
የቁርኣን ፀጋ 131
ሙእሚን አይዋሽም 134

ከፍ ሲሉ ወደታች መመልከት ... 136
እንዲህ ይጫወቱብናል ... 138
መጥፎ ሚስጢርህን ... 139
ዱንያ - ጥሎ ማለፍ ... 141
አርባ ለደረሰ ሰው ... 144
መንጋነት ይውደም ... 145
እኛ ከአላህ ነን ለአላህ ነን 148
ደወል (2) ... 151
የአለማወቅ ጣጣ 152
የክብር ትግል 155
ከዲን ፈተና ወዲያ ... 156
ለሌሎች መኖርን መልመድ ... 157
ክፍል ሁለት ... 158
አንዳንድ ሀሳቦች ... 158
ተመልሰናል (3) ... 193
የቤት ሰላም ... 195
ኑዛዜ 196
የአዘጋጁ የከዚህ ቀደም ሥራዎች ... 197
አመሰግናለሁ 199

መቅድም

ቢስሚላሂ ረሕማኒ ረሒም፣ አልሐምዱ ሊላሂ ረቢልዓለሚን፤ ወሶላቱ ወሰላሙ ዐላ ሲይዲል ሙርሰሊን፣ ነቢይና መሐመዲን ወአላ አሊሂ ወሶሕቢሂ አጅመዒን::

ኢማሙ ሻፊዒይ አላህ ይዘንላቸዉና በሞቱ ጊዘ ተማሪያቸው በህልም አያቸዉና "አላህ እንዴት አደረገዎ ኢማማችን ሆይ?" አላቸው አሉ::

"በአላህ እምላለሁ አላህ ማረኝ፣ አዘነልኝ፤ እንደ ሙሽራ ተደርጌ ወደ ጀነትም ተሸኘሁኝ::" አሉት::

"በምንድነው ይህን ዕድል ሊያገኙ የቻሉት ኢማማችን ሆይ?" አላቸው::

"እር-ሪሳላ በተሠኘው መጽሐፌ መግቢያ ላይ በፃፍኩት ጽሑፍ ነው::" አሉት::

ተማሪው ወዲያዉኑ ከእንቅልፉ ባነነ:: ብድግ ብሎ መጽሐፉን ፈለገና መግቢያዉን አየ:: በመግቢያው ላይም እንዲህ የሚል መልዕክት አነበበ::

"አል-ላሁምመ ሶልሊ ዐላ መሐመዲን ማ ዘከረሁ ዛኪሩን፤ ወሶልሊ ወሰሊም ዐለይህ ማ ገፈለ ዐን ዚከሪሂ አል-ጋፊሉን::"

"አላህ ሆይ አውሺዎች ባወሱት ቁጥር በሙሐመድ ላይ እዝነትህን አዉርድ፤ እርሣቸዉን ከማውሳት ዝንጉዎች በተዘናጉ ቁጥር በሙሐመድ ላይ እዝነትህንና ሰላምህን አዉርድ::"

ሶልለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም::

ሀሳብ ጭንቀታችሁ ሁሉ እንዲወገድ፣ ነገር ሁሉ ይገራላችሁ ዘንድ በነቢያችሁ ላይ ሶለዋት አዉርዱ::

ጽሑፍም ሆነ ማንኛዉንም መልካም ነገር ስትጀምሩ ለአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ምስጋና በማቅረብና በነቢያችሁ ላይ ሶላዋት በማውረድ ጀምሩ:: ጽሑፋችም ሆነ ጥረታችሁ የተባረከ ይሆናል፤ ከሰዎች ልብ ይደርሳል::

በአላህ ሥም ጀምረናል፤ እሱ ይቀበለን ይባርከልንም::

ሰዎችን በምንችለው ሁሉ ማገዝ ..

ጊዜው እንዴት ይሮጣል በረቢ!! መጽሐፍ ማሳተም ከጀመርኩ 16 ዓመት በላይ ሆነኝ:: ራሴንም ሆነ ሌሎችን እጠቅም እንደሆነ ብዬ ይኸው እጽፋለሁ:: አላህ ያመላከተኝና ኑርበት ያለኝ መንገድ ነዉና የቻልኩትን ያህል እፍጨረጨራለሁ:: ማን ያውቃል አምላኬ ዘንድ የተመዘገበልኝ መልካም ሥራ ይኸው ብቻ ሊሆን ይችላል::

ጌታዬ ሆይ! ከስንፍናዬ እና ከድክመቴ የተነሳ የምጽፈዉንና የምናገረዉን ባልሠራበት እንኳ ወደ መልካም ነገር ያመላከተ ሰው ከሚያገኘው ምንዳ አታሳጣኝ:: ልፋቴና ድካሜ ሁሉ ባዶ እንዳይቀር ተስፋዬ ሁሉ ባንተ ላይ ነው:: ባርያህ ነኝና እዝነትህን ሁሌም እከጅላለሁ::

ወዳጄ ሆይ! የዚህ ዓይነቱ ሥራ በጎ ነዉና አንተም ብትሠማራበት ብዬ ተመኘሁልህ:: ደግ ነገርን ለሌላው ሰው መመኘት ሌላ የምንዳ ማግኛ መንገድ ነው:: ወደመልካም ነገር ያመላከተም ልክ እንደሠሪው ነው:: እናም አስብበትና ሞክር:: አንተም ምንዳው ይበዛልህ ዘንድ:: ከዚህ አንፃር ለራስህ ያነሰ ግምት አትስጥ:: ማገልገል ኣችላለሁ በልና ተነስ::

አንድ ምሳሌ ልስጥህማ ... የነቢዩን ሶ.ዐ.ወ. ሙአዚን ዐይነልበሲሩን ዐብደላህ ኢብኑ ኡሚ መክቱምን ረ.ዐ. ታውቅ የለ!:: አዎ እሱ በአንድ ወቅት በሆነ ጦርነት ላይ ከሙስሊሞች ጋር ለመሳተፍ ብሎ ወጣ:: ሰዎችም "ዐይነሥዉር እኮ ነህ ምን ልትሠራ ለጂሃድ ወጣህ?" አሉት:: ኢብኑ ኡሚ መክቱምም "ቢያንስ የሙስሊሙን ቁጥር አበዛለሁ::" አላቸው:: የሙስሊሙ ቁጥር በጠላት ዐይን ብዙ መስሎ እንዲታይ አስቤ ነው::

ታዲያ ወዳጆቼ ... ከዚህ በላይ ሞራል አለ ወይ?:: ከዚህ በላይ ለኢስላም እና ለሙስሊሙ ማሰብ ይኖራል ወይ?:: ከዚህ በላይ የኃላፊነት መሰማት አለ ወይ?:: ዐብደላህ ጂሃድ ግዴታ ያልሆነበት፤ እንዲቀርም ምክንያት የተደረገለት ሰው ነው:: ነገርግን አይወጅብኝም ብሎ እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም:: ግዴታው የተነሳለት ቢሆንም ሀሳቡ አላረፈም:: በቻልኩትና ባገኘሁት መንገድ ሁሉ እስልምናን ልጥቀም ብሎ ከሙስሊሞች ጋር ተሰለፈ:: በታየው ልክ ኢስላምን እና ሙስሊሙን ላግዝ ብሎ ተነሳ:: የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የዓላማ ከፍ ማለትን ያሳያል፤ ለኢስላም የተቆርቋሪነት ስሜት ምን ያህል እንደሆነ ያንፀባርቃል::

ወዳጆቼ ... እኛም ከኢስላም እና ከሙስሊሙ አንጻር እንዲሁ እንደ ዐብደላህ ማሰብ ይኖርብናል። አላህ ሱ.ወ. ሙሉ አካል ሠጥቶናል። አዕምሮና ዕውቀት ለግሦናል። ስለዚህ ከዐብደላህ ያነሰ ሚና ሊኖረን አይገባም። ሀሳባችን ከፍ ያለ መሆን አለበት። ኢስላም የጉዳያችን ሁሉ አውራ ሊሆን ይገባል። ምንም ይሁን ምን ሚናችንን ማሳነስ የለብንም። አስተዋጽአዎችን ልናጣጥል አይገባም። ትንሽ ትልቅ ሳንል ሰዉን መጥቀም በምንችልበት መንገድ ሁሉ እንጥቀም።

ወዳጄ ሆይ! ለቦታው አልመጥንም፣ ተገቢ ሰዉም አይደለሁም ብለህ ሳትፈራና ሳትሸማቀቅ ወደ አላህ መንገድ እንድትጣራና መልካም ነገር ትጽፍ ዘንድ እመክርሃለሁ። ከአንደበትህ የሚወጣዉን በጎ ነገር አሳንሰህ እንዳታይ። የምትሠራዉን መልካም ነገር ዋጋዉን አታናንቅ። መልካም ቃል ሰዉን ይጠቅማል እንጂ አይጎዳዉም፣ በጎ ምክርም ያነሳል እንጂ አይጥልም።

ወዳጄ ሆይ! በዚህ መንገድ ሰዎችን እንድንጠቅም ላስቻለን አላህ ሱ.ወ. ምስጋና ይገባው። ጽሑፍን ላስተማረን አላህ ገለታ ይድረሰው። ፊደልንና ቃልን ለሠጠን አላህ ሐምድ ይሁን። ቃል ያቆማል፣ ቃል ያበረታል፣ ቃል ያፀናል። እንደዋዛ ከአንደበትህ በወጣች አንዲት ቃል የተነሳ አንድ ሰው መስተካከሉ፣ ማስታወሱ፣ መቃናቱ፣ መነቃቃቱ፣ መጥጠገኑ፣ መታረሙ፣ ወደ አላህ መመለሱ፣ መዝናናቱ፣ መረጋጋቱ፣ እፎይ ማለቱ፣ መተንፈሱ፣ ተስፋ ማድረጉ፣ .... ምንዳው ቀላል እንዳይመስልህ።

ወዳጄ .. የዓለም ዋና እሴቷ ሰው ነው። የፈጥረተዓለሙ አንጡራ ሀብት የአደም ልጅ ነው። የተከበረዉና የላቀው ትልቁ ፍጠሯ እኔ፣ አንተና አንቺ ነን። ስለሆነም ስለሰው በእጅጉ ማሰብና መጨነቅ ይኖርብናል። ይህን የተከበረ ፍጡር በቻልነው ሁሉ ማገዝ አለብን። ሰዉን አገዝን ማለት ራሣችንን አገዝን ማለት ነው። ለሰው ስናስብ አላህ ያስብልናል። ሰዉን ስናቆም አላህ ያቆመናል፣ ሰዉን ስናቀና አላህ ያቀናናል፣ ሰዉን ስንወድ አላህ ይወደናል፣ ሰዉን ስንደግፍ አላህ ያዝንልናል፣ ለሰው ስንኖር አላህ ያኖረናል። ረሱላችን እንዳሉትም ምርጡ ሰው ለሰው ጠቃሚ የሆነው ነው። ለሰው መኖርን እንልመድ።

ሰዎችን ከምናግዝባቸው መንገዶች መካከል ዋናው እና ትልቁ ወደ ኢስላም እንዲመጡ ጥሪ ማድረግና ለመስተካከላቸው ምክንያት መሆን ነው።

ሰባሐል ኸይር!!

አቀራረብን ማሳመር ...

ኮምጣጤና ማር የሚሸጡ ሁለት ሰዎች ነበሩ። ብዙ ሰዎች የማሩን ባለቤት ትተው ከኮምጣጤው ባለቤት ይገዙ ነበር። ይህን ያስተዋለው ማር ሻጭ አንድ ቀን ባልደረባዉን ጠየቀ። "ሰዎች የኔን ማር ትተው ወደ ኮምጣጤህ የሚያዘነብሉበት ምክንያቱ ምንድነው?" አለው።

ኮምጣጤ ሻጩም መለሠለት። "እኔ ኮምጣጤዬን በማር ምላስ ነው የምሸጠው፤ አንተ ግን ማርን የመሠለ ዕቃ በኮምጣጤ ምላስ እየሸጥክ ነው።" አለው።

ዕቃህ በርግጥ ጥሩ ነው ግና አቀራረብህ ትከክል አይደለም ማለቱ ነበር። አዎን አንዳንድ ጊዜ ሸቀጣችን ምርጥ ከመሆኑ ጋር አቀራረባችን ሰዎች እንዲርቁን፣ ጥሩ ሥም እንዳይኖረንና ደንበኞችን እንዳናፈራ ሊያደርግ ይችላል። ወዳጄ! በግብይት ዓለም ጥሩ ዕቃ ይዣለሁ ሰው ይገዛኛል ብለህ አትኮፈስ። በርግጥ ዕቃ መያዝ መልካም ቢሆንም ቁምነገሩ ዕቃ መያዝህ ብቻ አይደለም። አሻሻጡን እና አቀራረቡን ካልቻልክበት ኪሣራ ነው። ብዙ ቦታ ላይ የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የእስልምናችን ዕጣፈንታ ሆኖ እናያለን። ሃይማኖቱ ምርጥ ሃይማኖት ሆኖ ሳለ በተከታዮቹ ባህሪና አቀራረብ የተነሳ ገጽታው ተበላሽቶ እናገኛለን። ምርጡ አስተምህሮ በአቀራረብ መከፋት ተሸፍኖ ሰዎች እስልምናን ሲፈሩት እንታዘባለን።

እናም ወዳጄ! ምርጡን እስልምና መያዝህን ብቻ አትመልከት። ተሠጥቶኛል ብለህ ዲንህን ለራስህ ብቻ አትኑርበት። እንዴት ለማኅበረሰቡ ማቅረብ እንዳለብህ አስብበት፣ አቀራረቡንም እወቅበት። ማስተላለፉን ቻልበት። ቻይኖች "ፈገግታ ካልቻልክ ሱቅ አትክፈት።" ይላሉ።

እስልምናችን ምርጥ ሀብት ነው። ለሌሎች ልንመኘው የሚገባ ትልቅ ክብረት ነው። በሁሉም ሰው ቤት መኖር ያለበት፤ በገንዘብ ሊተመን የማይችል ግዙፍ በረከት ነው። ይህን ሀብት፣ ክብረትና በረከት ለሌሎች ለማስተላለፍና እንዲጠቀሙበት ለማድረግ የቻልነዉን ያህል ጥረት ማድረግ ይኖርብናል።

ወዳጆቼ! እኛ በምድር ላይ የአላህ ወኪሎች፣ የኢስላም አምባሳደሮች፣ የደግ ነገር አስተላላፊ ኮሪደሮች ነን። እኛ የዲኑ አገልጋዮች እና መልዕክተኞች ነን። በኛ በኩል ነው ዲናችን ወደሌሎች የሚደርሰው። በኛው በኩል ሰዎች ሁሉ ስለዚህ ዲን መልካምነትና ዉብ አስተምህሮው ሊያውቁ ይገባል። ይህም ግዴታችን ነው።

አላህ ሱ.ወ. ሰዎችን ወደ መልካም ነገር እንድንጠራ፣ ከመጥፎም ሁሉ እንድናስጠነቅቅ አዞናል። በዚህ ረገድ ግዴታችንን ካወቅን ለአቀራረባችን ደግሞ ማሰብና መጠንቀቅ ይኖርብናል። አቀራረብን ማሳመር ለዲን ማስብ፣ ለትበላው መጓጓት ነዉና። ወዳጆቼ! ሰዎች ከዲናችን በፊት እኛን ያያሉ። የእኛን ሁኔታ በማየትም ወደ ዲናችን ይሳባሉ ወይም ደግሞ ይሸሻሉ። እዎ ዓለም ላይ ማንም የለለዉን ምርጡንና ዉዱን ሃይማኖት ይዘናል። እሱን ለማስተማርና ለማሳወቅ አቀራረባችን ምን ይመስላል ብለን መፈተሽ ይኖርብናል። በባህርያችን መበላሸትና በሙጥፎ አቀራረባችን የተነሳ ስንቱ ሰው ዲናችንን እንዳይቀበለው አከል ሆነናል። ጥሩ አስተምህሮ ይዘን አቀራረባችን በመከፋቱ ብቻ ስንቱ ሸሸን!። ስንቱ ሰው በዚህ መልኩ አልቀበለዉም፣ ዲን እንዲህ ከሆነ ይቅርብኝ ብሎ ራቀን። ኢስላም ለሥነምግባር ትልቅ ትኩረት ሠጥቷል። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) "በጅነት ዉስጥ ወደኔ ቀርበው የሚቀመጡት የመልካም ሥነምግባር ባለቤቶች ናቸው።" ብለዋል። "ወደዚህ ምድር የመጣሁበት ዋና ዓላማ መልካም ሥነምግባራትን ላሟላ ነው።" ብለዋል። "አፈጣጠሬን ያሳመርከ አላህ ሆይ ባህሪዬንም አሳምር" እያሉ ዱዓ ያደርጉ ብዙ ጊዜ ይሰሙ ነበር። መልካም ሥነምግባር ስንል ትህትና፣ ፈገግታ፣ መልካም ንግግር፣ እውነተኛነት የመሳሠሉትን ነው።

ወዳጄ! አንደ ዩሱፍ ቆንጆ ብትሆን እንኳ ሥነምግባርህ ካላማረ ባዶ ነህ። አቀራረብና ፀባይህን ማሳመር ላንተም ለዲንህም ይጠቅማል። ነቢያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ብዙዎችን ወደ ዲኑ ያመጡት ባማረ ባህርያቸው ነው። አቀራረብህ ሲያምር ሰዎች ይቀማመጡልሃል፣ ይሰበሰቡልሃል። አላህም ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) **" ዐመለ መጥፎ ልበደረቅም በሆንክ ኖሮ ከዙርያህ በተበተኑ ነበር።"** ብሏቸዋል። በርሣቸው ገር ባህሪ አስልምና ከኛ ደረሰ። አስልምና አሩቅ ምሥራቅ አገራት ድረስ የዘለቀው አቀራረቡን ማሳመር በቻሉበት ደጋግ ሙስሊሞች ነው።

አንዳንድ ሰዎች በአቀራረባቸው ቁምነገርንና መልካም ነገርን ያስጠላሉ፣ ሌሎች ደግሞ በአቀራረባቸው የማይረባን ነገር ቁምነገር ያደርጋሉ። ዉሸት ይዘው በአቀራረብ ብቻ ያሳመኑ ብዙ አሉ፣ እውነት ይዘው አቀራረባቸው በመከፋቱ ሰዎች ያልተቀበሏቸው አሉ። ቆንጆ ዕቃህን በንግግርህ አታበላሽ፣ በገረጮራጫ ፀባይህ ሸቀጥህን አትጣል። አላህ (ሱ.ወ.) አንድ ሰው ሥራዉን ሲሠራው አሳምሮ ይሠራው ዘንድ ይወዳል። የይድረስ ይድረስ ሳይሆን አሳምረህ፣ ተጠበህና ተጨንቀህ ፃፍ፣ ተናገር፣ አስተምር። የማሳመር ጉዳይ ይህንን መጽሐፍንም ይጨምራል፣ አዘጋጁ የቻለዉን ያህል ተጠቢል ተጨንቋልና ዱዓ አድርጉለት።